በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

ለአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

አላጌ

ጉዳዩ፡- **የኮሌጁን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤**

በርዕሱ የተጠቀሰውን የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 21 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 17 ገጽ አባሪ በድምሩ 38 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል፡፡ በመሆኑም በገጽ 39 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከ38 ገጽ አባሪ ጋር
- ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከ38 ገጽ አባሪ ጋር

አዲስ አበባ

በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በቀድሞው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱና የኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

የማሻሻያ ሃሳቦች

የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.1/14/6 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኮሌጁ የካቲት 30 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር አላጌ/አስ/8/15/773 በጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ተሰብሳቢ ሂሳብ

1.1 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

1.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና ኮሌጁ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ ከካፒታልና ከውስጥ ገቢ በጀት በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

1. ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 184,444.73፣
2. ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 507,217.05፣
3. ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 232,681.10፣

በድምሩ ብር 924,342.88 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) በአብዛኛው ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል። ስለሁኔታው ቀደም ካሉት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ጀምሮ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በአሁኑ ኦዲት ወቅትም ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ሂሳቡ ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰቡ) ይገኛሉ። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2 ሥጋት

- ☞ በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፡፡
- ☞ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 184,444.73፤

   1.1. በሂሣብ መደብ 4211 የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 167,852.86 ቀደም ሲል በገለጽነው መሠረት ለዋናው መሥሪያ ቤት በደብዳቤ አሳውቀን ምላሽ አልተሰጠንም፡፡ ሆኖም ግን በቃል እየደሄዱበት ለመሆኑ ገልጸውልናል፡፡

   1.2. በሂሣብ መደብ 4209 የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 16,591.87 ደግሞ የሀር ትል ፕሮጀክት ሠራተኞች በኮንትራት ተቀጥሮ የተከፈለ ሲሆን እንዲተካልን ጠይቀን ፕሮጀክቱ የተዘጋ በመሆኑ ሊተካልን አልተቻለም፡፡ በዚሁ መሠረት ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ለመጨረሻ ያለብን ችግር ገልጸን የምንጽፍ ሲሆን በዚያው የመፍትሂ አቅጣጫ እንዲሰጡን የምንጠይቅ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2. ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 507,217.05፤

   2.1. ብር 30,897.50 ቀደም ሲል በገለጽነው መሠረት ለዋናው መሥሪያ ቤት በደብዳቤ አሳውቀን ምላሽ አልተሰጠንም፡፡ ሆኖም ግን በቃል እየደሄዱበት ለመሆኑ ገልጸውልናል፡፡

2.2. ብር 41,499.97 ቀደም ሲል እንዳሳወቅነው በአመዘጋገብ ስህተት በተፈጠረው ችግር ምክንያት ተሰብሳቢ ሊሆን ችሏል። ይህንን ለማስታረቅ ከአቅማችን በላይ በመሆኑ ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሙያዎች በደብዳቤ በማሳወቅ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጡን የምንጠይቅና የምንከታተለው መሆኑን እንገልጻለን።

2.3. ብር 385,433.00 ከውስጥ ገቢ ለተማሪዎች ቀለብ የሚውል በዱቤ ተሸጦ ሳይከፈል የቀረ ሲሆን አሁን ላይ ለመክፈል በጀት የሌለን በመሆኑ ይህንንም ችግር ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በደብዳቤ በማሳወቅ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጡን የምንጠይቅና የምንከታተለው መሆኑን እንገልጻለን።

2.4. ቀሪውን ብር 49,386.58 የምንሰበሰብ መሆኑን እንገልጻለን።

3. <u>ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 232,681.10</u>፤

3.1. ብር 206,555.32 ተሰብሳቢ ሂሣብ ቀደም ሲል የኮሌጁ ሠራተኞች ገንዘብ ያዥ ሆነው ይሠሩ የነበሩ ሠራተኛ የገንዘብ ጉድለት ስለተገኘባቸው ይህን የተገኘባቸው ጉድለት ክስ ተመስርቶባቸው በክሱ መሠረት ፍርድ ቤቱ ከወር ደመወዛቸው ላይ ተቀናሽ በማድረግ ተመላሽ እንዲያደርጉ በወሰነው መሠረት ሰራተኛው ከደመወዛቸው ላይ እየቀነሰ ሳለ እንደገና በህግ ጥላ ስር በመዳረጋቸው ገንዘቡ ሊሰበሰብ አልቻለም። ይህንን አስመልክቶ ለዋናው መሥሪያ ቤት በደብዳቤ ያሳወቅን መሆኑን እየገለጽን ለዋና መስሪያ ቤት የተጻፈውን ኮፒ አድርገን አያይዘናል።

3.2. ቀሪው ብር 26,125.78 ከ10 ዓመት በፊት ከቶታል ኢትዮጵያ ጋር የነዳጅ ሂሣብ ተከፍሎ ቀሪ ሂሣብ ሲሆን፣ ይህንን ሂሣብ በተደጋጋሚ ድርጅት እንዲመለስ ተጠይቆ ምላሽ ባለመገኘቱ ሂሣቡን ለማስታረቅ ተቸግርናል። በመሆኑም ሂሣቡ ስለቆየና መፍትሄ ያጣንለት ስለሆነ ለሚመለከተው ከመዝገብ እንዲሰረዝልን በደብዳቤ የምንጠይቅ መሆኑን እንገልጻለን።

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ በአብዛኛዎቹ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለሉ የመጡ ሲሆን ባለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠባቸው ከመሆናቸው አንጻር ኮሌጁ የተሰብሳቢ ሂሳቦቹን ሁኔታ አጣርቶ በመመሪያው መሰረት እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉት ደግሞ እንዲሰረዙ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ አጥጋቢ አይደለም። ስለሆነም በተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ መወራረድ (መሰብሰብ) የሚችሉት እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉት ደግሞ መመሪያውን ተከትሎ እንዲሰረዙ መድረግ ይኖርበታል።

2. የወጪ ሂሳብ

2.1. አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ፤

2.1.1. ግኝት

ኮሌጁ አዲስ ለሚቀጥራቸው ሠራተኞች የከፈለው ደመወዝ ከተቀጠሩበት ቀን ጀምሮ መሆኑንና የለቀቁት ሠራተኞች ደግሞ ላልሰሩበት ጊዜ ክፍያ አለመፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሶስት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ በጠቅላላው ብር 4,728.72 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

2.1.2. ሥጋት

- መመሪያን ተከትሎ አለመስራት ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል።
- የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ከኮሌጁ ከሥራ ለቀው ከሄዱ በኋላ የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም በደመወዝ አከፋፈል ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን።

2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

አላግባብ የተፈጸመ ደመወዝ ክፍያ ተመላሽ እንዲያደርጉ ለሠራተኞቹ በአድራሻቸው ደብዳቤ ተጽፎ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

2.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 12(1ሀ) መሰረት ለደመወዝ ዝግጅት ሊሟሉ ከሚገባቸው መረጃዎች ውስጥ አንዱ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የሥራ ክፍሎቹ ይህንን መረጃ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል በግልባጭም የአስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ማሳወቅ እንዳለባቸው ተመልክቷል። በኮሌጁ ይህ አሰራር ባለመተግበሩ ምክንያት ያለአግባብ የደመወዝ ክፍያ ሊፈጸም ችሏል። ስለሆነም በቀጣይ የሥራ ክፍሎቹ በመመሪያው መሰረት ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን እንዲሳውቁ፤ አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ተገቢው ክትትል ተደርጎ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

3. ንብረት

3.1 አቅራቢው በውሉ ግዴታው መሰረት ጤፉን ያላቀረበ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ፤

3.1.1. ግኝት

ኮሌጁ ለሚገዛቸው እህሎች ተገቢውን ውል መግባቱንና በውሉ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ ከየሱፍ ሂርጶ ለመግዛት መስከረም 29/2008 ውል የተዋዋለ ሲሆን በውሉ ተራ ቁጥር 6 አቅራቢው የምግብ ጥሬ እቃዎቹን በውድድር ወቅት ባቀረበው ናሙና መሰረት በሚፈለገው ጥራት 1ኛ ደረጃ ለግዢ ፈጻሚው ለማቅረብ ግዴታ ገብቷል። ከዚህም በተጨማሪ በውሉ ተራ ቁጥር 11 ደግሞ አቅራቢው የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱ የምግብ ጥሬ

እቃዎቹን በገባው ውል በሚፈለገው ጥራት ባቀረበው ናሙና መሰረት ባለማቅረቡ በግዢ ፈጻሚው ላይ ጉዳት ካደረሰበት የተያዘው የዋስትና ገንዘብ ማለትም ብር 512,400.00 ለግዢ ፈጻሚው ገቢ እንደሚደርግ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል፡፡ ነገር ግን የሱፍ ሂርጶ በ2008 ዓ.ም. በተለያዩ ጊዚያት ካቀረባቸው 1,565.69 ኩንታል ጤፍ ውስጥ 325 ኩንታል የሚሆን የተበላሸ ወይም ከአሸዋ ጋር የተቀላቀለ ጤፍ ቢሆንም ኮሌጁ ጤፉን ለአቅራቢው በጊዜው መመለስ አሊያም በፍርድ ቤት ከሶ አቅራቢው ለዋስትና ካስያዘው ብር 512,400.00 ውስጥ እንዲከፈለው መጠየቅ ሲገባው ኮሌጁ ብር 416,325.00 በውሉ መሰረት ላልቀረበለት ጤፍ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን በዚሁ ምክንያት 325 ኩንታል ጤፍ ያለአገልግሎት በኮሌጁ ወፍጮ ቤት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.1.2. ***ሥጋት***

- ☞ ክፍያዎች በውሉ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

3.1.3. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

ኮሌጁ በውሉ መሰረት ያለአግባብ የወጣውን ወጪ እንዲመለስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ጥንቃቄ ሊያደረግ ይገባል፡፡

3.1.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

ኮሌጁ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በጹሁፍ ባቀረበው ቅሬታ ላይ አቅራቢው እንዲቀጣ ተደርጓል፡፡ 227.69 ኩንታል ጤፍ ቀጭ ቀጭ ስላለው ለተማሪዎች ምግብነት ለማቅረብ አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ጤፉን ለብዙ ጊዜ ማስቀመጡ አግባብ ስላልሆነ፣ ህዳር 13 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር አላጌ/አል37/21/584 ኮሚቴ በማቋቋም በሽያጭ እንዲወገድ የዋጋ ተማኝ ኮሚቴ አቋቁመን የኮሚቴውን ሪፖርት እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡ በሌላ በኩል ግለሰቡ

ላደረሰብን ጥፋት (በደል) በኮሌጁ ሕግ አገልግሎት በኩል በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት በሕግ ለመጠየቅ አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ነው።

3.2 <u>በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች፤</u>

3.2.1. <u>ግኝት</u>

የኮሌጁ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

I. <u>በጋራዥ የሚገኝ የመኪና ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

1. በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ጎማዎች አገልግሎት ከማይሰጡ የመኪና ተመላሽ መለዋወጫዎች ጋር ተከማችተው ከመቀመጣቸው በተጨማሪ እስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
2. በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 17 የሞተር ሳይክሎች፣ 215 የመኪና እና የትራክተር ጎማዎች፣ ከ20 በላይ የሞተር ሳይክል ጎማዎች፣ ጀኔሬተር፣ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ 1 ቤለር፣ 2 ዶዘሮችና 1 ኮምባይነር ያለ አገልግሎት ከአንድ ዓመት በላይ ፀሃይና ዝናብ እየተፈራረቀበት የሚገኝ መሆኑ፤
3. በግምጃ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፤

II. <u>የመድኃኒት ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

1. በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
2. በግምጃ ቤቱ ውሰጥ የመድኃኒት ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ (እስቶክ ካርድ) መዝገብ ያልተቋመ መሆኑና ምዝገባ የማይከናውን መሆኑ፤

III. <u>የአላቂና ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

1. በግምጃ ቤቱ በድምሩ ብር 2,350.00 የሚያወጣ ከአንበሳ ጫማ ፋብሪካ የተገዛ 4 አጭርና 1 ረጅም የወንድ ቆዳ ጫማ ያለአገልግሎት ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤

2. በግምጃ ቤቱ ከ 570 በላይ የሚሆኑ የወንድ ሸራ ጫማዎች ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤

3. በግምጃ ቤቱ ብዛት ያላቸው በኢትዮጵያ ህጻናት አንባ ስም የታተሙ ደረሰኞች ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤

4. በግምጃ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፤

IV. <u>የተማሪዎች ወፍጮ ቤት</u>፤

1. በወፍጮ ቤቱ ውስጥ ሁለት የኮሌጁ ሳይክሎች ለበርካታ ዓመታት ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

2. በወፍጮ ቤቱ ከ30 ጆንያ በላይ የሚሆኑ ደረሰኞች ከ20 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

3. በወፍጮ ቤቱ ከ25 ማዳበሪያ በላይ የሚሆኑ የማያገለግሉ መጽሐፍቶች ከ20 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4. በወፍጮ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፣

V. <u>የአብጀታ ካምፓስ የተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

1. በግምጃ ቤቱ 5 ፍሪጅ፣ 15 የእሳት አደጋ መከላከያ፣ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣1 የወርቅ ሚዛን፣ 1 ዲፕ ፍሪጅእና 103 የመኪና ጎማ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

2. በግምጃ ቤቱ የኮሌጁ ንብረት የሆኑ ከ100 በላይ የሚሆኑ ጎማዎችና ብረታ ብረቶች ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሌጅ ሰልጣኞች ንብረት ጋር ተቀላቅሎ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤

VI. <u>የአሳማ እርባታን በተመለከተ</u>፤

1. 16 ማዳበሪያ የተመረዘ የአሳማ መኖ ካልተበላሸ የአሳማ መኖ ጋር በአንድ ላይ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
2. በአሳማ መኖ ማቀነባበሪያ ውስጥ የሚሰሩት ባለሙያ ባለመሆናቸው ምክንያት በተሰራ ስህተት የተመረዘ መኖ በመመገባቸው ከ70 በላይ የሚሆኑ አሳማዎች መሞታቸው፤

VII. በዘርዓይድረስ ንብ እርባታ ከ27 በላይ የሚሆኑ የንብ ቀፎዎች ቢኖሩም ቀፎዎቹ በአግባቡ አለመያዛቸውና ቦታውም ለንቦቹ አመቺ አለመሆኑ፤

ታውቋል። ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም በአብዛኛዎቹ ላይ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱን ለመገንዘብ ተችሏል።
(በብልሽት ለሚገኙት ዕቃዎች የፎቶግራፍ አባሪ 6 ተያይዟል)

3.2.2. <u>ሥጋት</u>

☞ ኮሌጁ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።

☞ የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

3.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የኮሌጁ ሥራ አመራር በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሰረት በአስቸኳይ ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። እንዲሁም የኮሌጁን ማህበረሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት ማግኘት ይችል ዘንድ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ንብረቶች እንዲጠገኑ መጠገን የማይችሉት ደግሞ መንግሥት

ያወጣውን የንብረት አወጋገድ መመሪያ ተከትለው እንዲወገዱ ብርቱ ጥረት ሊደረግ ይገባል።

3.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

I. በጋራዥ የሚገኝ የመኪና ዕቃ ግምጃ ቤት፤

1. ጎማዎቹ ለትራክተሮች ከዋና ግምጃ ቤት የወጡ ሲሆን፣ ትራክተሮች በመበላሸታቸው እስኪጠገኑ ድረስ ከመለዋወጫዎቹ ጋር የተቀመጡ መሆኑ ተገቢ ስላልሆነ፣ ለይተን አስቀምጠናል። ትራክተሮቹም እየተጠገኑ ስለሆነ እንደተሠሩ ሥራ ላይ እናውላለን።

2. 17 የሞተር ብስክሌት በመለዋወጫ ችግር የቆሙ ስለሆነ፣ መለዋወጫ እንደተገኘላቸው ተጠግነው ሥራ ላይ ይውላሉ። ካልሆነም ይወገዳሉ። 215 የመኪና እና የትራክተር ጎማዎች ከ20 በላይ የሞተር ሳይክል ጎማዎች በተመለከተ የሚወገደው የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ስለሆነ፣ ሪፖርት ተደርጎላቸው ውሳኔ እየተጠባበቅን እንገኛለን። ጄኔሬተር፣ ቤለር፣ ዶዘሮች እና ከምባይነር በብልሽት የቆሙ ስለሆነ፣ መለዋወጫ እንደተገኘላቸው ተጠግነው ሥራ ላይ ይውላሉ። እስፔርፓርት ካልተገኘ እንዲወገዱ ይደረጋል።

II. የመድኃኒት ዕቃ ግምጃ ቤት፤

1. ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች ኮሚቴ በማቋቋም እንዲወገድ ተደርጓል።

2. የመድኃኒት ግምጃ ቤቱ ሚኒ ግምጃ ቤት በመሆኑ እና ከዋና ግምጃ ቤት በሞዴል 22 ወጪ ያደርግ ስለነበር ሞዴል 19 አይጠቀምም ነበር። እስቶክ ካርድ አልተከፈተለትም። ይሁን እንጂ በተሰጠን አስተያየት መሠረት ግምጃ ቤቱ በግዥም ይሁን በእርዳታ የሚገቡትን እራሱን ችሎ በሞዴል 19 ገቢ በማድረግ በ22 ወጪ አድርጎ እንዲያስራጭ ተደርጓል። በተጨማሪም ቢን ካርድ እና እስቶክ ካርድ ተከፍቶለት የቁጥጥር ሥራው እንዲከናወን ተደርጓል።

III. <u>የአላቂና ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

1. ከአንበሳ ጫማ ፋብሪካ ጋር በመነጋገር እንዲቀይሩልን ጥያቄ አቅርበን ለጊዜው ምርቱን አቁመናል ማምረት እንደጀመርን እንቀይርላችኋላን ስለአሉን እየተከታታልን ነው፡፡
2. ለተማሪዎች ተገዝቶ ሲታደል የተረፈ በመሆኑና ቁጥሩ ትንንሽ ስለሆነ ምንም ድጋፍ ለሌላቸው የዕውቀት ፋና ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡
3. ሰነዶቹ ለኮሌጁ ምንም ግልጋሎት የማይሰጡ ስለሆነ፣ እንዲወገዱ ተደርገዋል፡፡
4. ቀደም ሲል የነበረው የእሳት መከላከያ የተበላሸ ስለሆነ ግምጃ ቤቱን ያለ እሳት አደጋ መከላከያ መጠቀሙ አግባብ ስላልሆነ የተሰጠንን አስተየየት በመቀበል ተገዝቶ እንዲቀርብ መመሪያ የተሰጠ ስለሆነ፣ አፈጻጸሙን እየተከታተልን ነው፡፡

IV. <u>የተማሪዎች ወፍጮ ቤት</u>፤

1. ብስክሌቶቹ ወደ ተመላሽ ግምጃ ቤት ገቢ ተደርገዋል፡፡ ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስገወድ ኤጀንሲ ሪፖርት ከተደረጉት ጋር ለማስወገድ እየተጠባበቅን ነው፡፡
2. ከ30 ጆንያ በላይ የሚሆኑ ደረሰኞች እና ከ25 ማዳበሪያ በላይ የሚሆኑ መጽሐፈቶች ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡
3. ለወፍጮ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መኖር እንዳለበት የተሰጠን አስተያየት ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ ለኮሌጁ የተለያዩ ግምጃ ቤቶች ግልጋሎት የሚውሉ በጨረታ እንዲገዛ ጨረታ የወጣ በመሆኑ ግዥው እንደተፈጸመ ለየግምጃ ቤቶቹ ይታደላል፡፡

V. <u>የአብጃታ ካምፓስ የተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

1. በግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ በኩል እንዲወገድልን ጎማ እና ፍሪጅ ዝርዝር ያቀረብን ስለሆነ ውሳኔ እንደተሰጠበት የእሳት አደጋ

መከላከያውንም አብረን በአንድ ላይ እናስወግዳለን። የወርቅ መመዘኛ ሚዛን ለእንስሳት ጤና ትምህርት ዘርፍ ተሰጥቷል።

2. ጎማዎቹ ተለይተው እንዲቀመጡ ተደርጓል። ብረታ ብረቶቹ ለእንጨትና ብረታ ብረት ወርክሾፕ ተሰጥተዋል።

VI. <u>የአሳማ እርባታን በተመለከተ</u>፤

1. የተመረዘው 16 ኩንታል መኖ በማቃጠል ተወግዷል።
2. በመኖ ማዘጋጃና ማከማቻ መጋዘን ውስጥ እርጥበት እንዳይከሰት በየእለቱ የመከታተል ሥራ ተጠናክሮ ተጀምሯል።

VII. በዘርዓይ ድረስ ንብ እርባታ ቀፎዎችንና አካባቢውን የማጽዳትና የማመቻቸት ሥራ ተከናውኗል። በበጋና በክረምት ንቦች ተጨማሪ መኖ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

3.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ኮሌጁ በንብረት አስተዳደሩ ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ የሚበረታታ ነው። ሆኖም እርምጃ ለመወሰዱ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል። ኮሌጁ በቀጣይም እርምጃ ባልተወሰደባቸው በንብረት አስተዳደር ላይ የታዩትን የአሰራር ክፍተቶች ለማረም አስፈላጊው ጥረትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል።

3.3 <u>የተሽከርካሪ ስምሪት፣ አያያዝና፣ አጠቃቀምና አወጋገድን በተመለከተ</u>፤

3.3.1. <u>ግኝት</u>

የኢንስቲትዩቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 34/2004 መሰረት እንዲሁም በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1. የሰሌዳ ቁጥር ኮድ UN-0965 ቶዮታ አውቶሞቢል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩ የ "UN Development Program" ሥም መሆኑ፤

2. **የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** 4 **ኢት**-05421 **እና ኮድ** 4 **ኢት**-10149 **ቶዮታ ሎንግ ቤዝ አውቶሞቢል ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤**
3. **አስር ሊብሬ የሌላቸው ሞተር ሳይክሎች መኖራቸው፤**
4. **ብዛታቸው** 22 **የሆኑ ቦክሰር ሞተር ሳይክሎች ሊብሬና የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤**

ታውቋል፡፡ (**ለዝርዝሩ አባሪ** 3 **ተያይዟል**)

3.3.2. ***ሥጋት***

☞ **በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡**

☞ **አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ ካልተደረጉ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡**

3.3.3. **የማሻሻያ ሃሳብ**

✓ **የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም ለሆኑ ተሽከርካሪዎቹ በኮሌጁ ሥም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲወጣላቸው፤**

✓ **ጌጅ የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው እንዲሰራ፤**

✓ **የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር** (**ሊቤሬ**) **እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር ለሌላቸው ሞተር ብስክሌቶች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር** (**ሊቢሬ**) **እና የሰሌዳ ቁጥር እንዲወጣላቸው እንዲደረግ፤**

እናሳስባለን፡፡

3.3.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

1. **የሰሌዳ ቁጥር ኮድ** UN-0965 **አውቶሞቢል መኪና ከግብርና ሚኒስቴር ለኮሌጁ ጉዳይ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት የተሰጠ ሲሆን ለግብርና የተሰጠውም በእርዳታ በመሆኑ ሊቢሬ የለውም፡፡**

2. የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4 ኢ.ት-05421 ሎንግ ቤዝ መኪና ጌጅ ለጊዜው የተበላሸ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቀት ጥገና ተደርጎለት ጌጁ እየሠራ ነው። የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4 ኢ.ት-10149 ማርቼዲስ መኪና ጌጅን በተመለከተ ደግሞ መኪናው አሮጌ ሞዴል በመሆኑ ከካምፓኒው መለዋወጫ ማግኘት ካለመቻላችን እና ከግለሰቦች ድርጅትና ጋራዥም ሊገኝ ባለመቻሉ ምክንያት ሳይቀየር ቆይቷል። ሆኖም አሁንም መለዋወጫ በማፈላለግ ለማሰራት ጥረታችንን ቀጥለናል።

3. ሊብሬ የለላቸው 10 ሞተር ብስክሌቶችን በተመለከተ ነሐሴ 2 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አላጌ/አላ21/24/598 በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ለግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ጠይቀን በየጊዜው ክትትል እያደረግን ነው።

4. ሊብሬ የሌላቸው ቦክስር ሞተር ሳይክሎችን በተመለከተ ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አላጌ/አላ21/28/581 ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እንዲሁም ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አላጌ/አላ21/58/582 ለሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ጠይቀን በየጊዜው ክትትል በማድረግ ላይ ነን።

3.3.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

1. ሊቢሬ ለሌለው መኪና አስፈላጊው መረጃ እንዲሟላ ተደርጎ ሊቢሬ እንዲወጣለት መደረግ ይኖርበታል።

2. ተጠግኖ ሥራ ላይ የዋለው ተሸከርካሪ አገልግሎት እየሰጠ ለመሆኑ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

3. ደብዳቤ መጻጻፍ ችግሮችን ለመፍታት የመጀመሪያ እርምጃ ቢሆንም ጉዳዩ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ኮሌጁ የበኩሉን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

4. በጀት

4.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

4.1.1. ግኝት

ለኮሌጁ የ2009 በጀት ዓመት ለካፒታልና ከውስጥ ገቢ ከተፈቀደለት የወጪ በጀት ውስጥ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ ሲታይ ፦

- ☞ ከካፒታል በጀት ብር 4,563,160.94፣
- ☞ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 11,429,727.50፣

በድምሩ ብር 15,992,888.44 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ ከካፒታል በጀት ደግሞ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ብር 171,056.42 ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

4.1.2. ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በኃላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. ከካፒታል በጀት ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት፡-
   - ♦ በቂ እና ሁኔታውን የጠቀበ ተወዳዳሪ (አቅራቢ) ባለመገኘቱ ምክንያት፣

- የማዕቀፍ ግዥ ዘግይቶ መድረስ፣ አሸናፊዎች ያሸነፉትን እቃዎች በወቅቱ ባለማቅረባቸው ምክንያት፣
- የገንዘብ ፈሰስ በወቅቱ ባለመቅረቡ ምክንያት፣

ሲሆን እነዚህ ችግሮችን በመለየት በቀጣይ የተሻለ አፈፃፀም (አጠቃቀም) ለማስመዝገብ እንቅስቃሴ የተጀመረ መሆኑን እንገልጻለን።
(በዝርዝር ለተሰጠው ምላሽ አባሪ 7 ተያይዟል)

2. ከውስጥ ገቢ ለበጀት አመቱ ከተፈቀደ በጀት ውስጥ ከ10% ብር 11,429,727.50 በላይ ሥራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት ኮሌጁ እንደሚታወቀው ለበጀት አመቱ ከውስጥ ገቢ ለወጪ በጀት የተፈቀዱልን በጀቶች ከተለያዩ ፋርሞች ምርት ሽያጭ የሚሰበሰብ በመሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች ለመሠብሠብ የታቀደው ገቢ ሳይሰበሰብ በመቅረቱ ምክንያት አጠቃቀማችንን ዝቅ እንዲል አድርጎታል።

4.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

- ኮሌጁ በተለያዩ ከአቅም በላይ ምክንያቶች ገቢውን በዕቅዱ መሰረት መሰብሰብ ካልቻለ ዕቅዱን በመከለስ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
- ከካፒታል በጀት ስለተራፊው ሂሳብ በዝርዝር የተሰጡት ምክንያቶች በአብዛኛው የዕቅድ ዝግጅቱ በቂ ጥናት ያልተደረገበት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል። በተጨማሪም የበጀት ዝግጅት ላይና አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መስሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

5. ልዩ ልዩ

5.1 በ2008 በጀት አመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደበት ግኝት፤

5.1.1. ግኝት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ኮሌጁ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በኮሌጁ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉ መሰረት የተፈጸመ እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኮሌጁ ከአፈወርቅ ግደይ ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት ለቢሮ ህንጻ እና ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የተፈጸሙ ክፍያዎች ኦዲት ሲደረጉ፡-
    - ☞ ብር **333,093.65** በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
    - ☞ ብር **25,444.35** ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣
    - ☞ ብር **633,083.09** ተቀንሶ ያልተመዘገበና ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
    - ☞ በተጠቀሱት ምክንያቶች ብር **325,433.79** ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣
    - ☞ አፈወርቅ ግደይ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ከግንቦት **16/2005** ጀምሮ ባሉት **360** ካላንደር ቀን ውስጥ ማለቅ እንዳለበት በውሉ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ሥራው ከ**840** ቀን (ለሁለት ዓመት ከሶስት ወር) በላይ የዘገየ መሆኑ፣ (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)
2. በ2006 በጀት ዓመት ለማስተባበሪያው ተልኮ የተወራረደው የ2005 በጀት አመት የወጪ ሂሳብ ብር 99,883.05 በ2006 በጀት አመትም በኮሌጁ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

ተገልጾ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት ወቅትም ግኝቶቹ ላይ ማስተካከያ ሳይደረግ ባሉበት ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል።

5.1.2. <u>ሥጋት</u>

ኮሌጁ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡-

- ☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

5.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል። ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

5.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. እስካሁን ድረስ ለስራ ተቋራጩ ክፍያ ያልተፈፀመ በመሆነ የተወሰደ እርምጃ የለም ነገር ግን በሚከፈለው ክፍያ ላይ በኦዲት የተሰጠንን ማስተካከያ የምንሰራ ሲሆን ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 25,444.35 የተባለውን ሂሳብ በድጋሚ ሲሰራ በመብለጥ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩን ያረጋገጥን ስለሆነ በሚከፈለው ክፍያ የሚስተካከል ይሆናል። የመያዣያ ሂሳብን ተቀንሶ ነገር ግን ያልተመዘገበ ሂሳብን በተመለከተ እስከአሁን የተቀነሰው ሂሳብ ወደ ትሬዠሪ ፈሰስ የሆነ ስለሆነ በምንከፍልበት በጀት አመት ተጠይቆ የሚከፈል በመሆኑ አሁን ላይ ማሳየት የሚቻል ስለሆነ በዚህ አግባብ ቢታይ እንላለን።
2. ከዋናው መሥሪያ (ከቲቪቲ) የካቲት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 18/መ/አጠ20/1/26 የማስተካከያ እርምጃ እንድንወሰድንና ማስተካከያውን እድንሰራ በጽሁፍ ያሳወቀን ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ለፋይናንስ ክፍል

ስላልተመራ ማስተካከያውን አልሰራንም። በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ እንወስዳለን።

5.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተቀነሰ እንጂ በመብለጥ የተቀነሰ አለመሆኑ በአባሪው በዝርዝር የሚታይ ነው። ስለሆነም በኮሌጁ ሊሰራ የታሰበው ማስተካከያ ላይ የበለጠ ስህተት ከመፈጸሙ በፊት ሂሳቡን በዝርዝር ማየትና ማስላት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በኦዲት የሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን በወቅቱ ተግባራዊ ማድረግ ኮሌጁን ለበለጠ ጥፋትና ብክነት እንዳይጋለጥ ስለሚረዳ ኮሌጁ በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኮሌጁ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!

አባሪ .1

<u>የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር</u>፤

ተራ ቁጥር	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ ጊዜ	የቆይታው ጊዜ				ድምር
			ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ	ከአስር ዓመት በላይ የቆየ	
I.	ከካፒታል በጀት						
1	4203	ከ1990 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ					
2	4209	ከ2006 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ		16,591.87			16,591.87
3	4211	ከ2005 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ		167,852.86			167,852.86
4	4254	ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ				26,125.78	26,125.78
5	4274	ከ2005 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ			30,897.50		30,897.50
ድምር				184,444.73	30,897.50	26,125.78	241,468.01
II.	ከውስጥ ገቢ በጀት						
1	4202	ከ2007 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ				206,555.32	206,555.32
2	4274	ከ2006 እስከ ሰኔ, 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ			476,319.55		476,319.55
ድምር					476,319.55	206,555.32	682,874.87
ጠቅላላ ድምር				184,444.73	507,217.05	232,681.10	924,342.88

አባሪ. 2

ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ የደመወዝ ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	የሠራተኛው ሥም	ከሥራ የለቀቁበት ቀን	የወር ደመወዝ	ከስራ ከለቀቁ በኋላ ደመወዙ የተከፈለበት ወር	በሥራ የቆዩበት የቀን ብዛት	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለው የቀን ብዛት	ሊከፈል የሚገባው የደመወዝ መጠን	በብልጫ የተከፈለ የደመወዝ
1	ዶ/ር አህመድ ሃሰን	18/12/08	4,461.00	የነሀሴ 2008 ዓ.ም የ13 ቀን ደመወዝ	17	13	2,527.90	1,933.10
2	አቶ በየነ ቡና	10/02/09	961.00	የጥቅምት 2009 ዓ.ም የ21 ቀን ደመወዝ	9	21	224.23	736.77
3	አቶ ማማሩ አበበ	20/07/09	5,615.00	የመጋቢት 2009 ዓ.ም የ11 ቀን ደመወዝ	19	11	3,556.15	2,058.85
	ድምር		**11,037.00**				**6,308.28**	**4,728.72**

አባሪ. 3

ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	የተሽከርካሪው ዓይነት	የተሽከርካሪው ታርጋ ቁጥር
1.	NISSAN UD	3 ኢ.ት-15983
2.	ኤኔትሪ የጭነት	4 ኢ.ት-05109
3.	YAMAHA	4 ኢ.ት-0772
4.	YAMAHA	4 ኢ.ት-4373
5.	YAMAHA	4 ኢ.ት-4383
6.	YAMAHA	4 ኢ.ት-4372
7.	YAMAHA	4 ኢ.ት-0785
8.	YAMAHA	4 ኢ.ት-0787
9.	YAMAHA	4 ኢ.ት-4382
10.	YAMAHA	4 ኢ.ት-4379

<u>ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተሰራበት</u>

<u>በጀት እና ከበጀት በላይ የወጣውን ሂሳብ የሚያሣይ ዝርዝር፤</u>

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት				የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ
		ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	በላይ የወጣ	በፐርሰንት በ(%)	
I. ከካፒታል ወጪ ሂሳብ በጀት		ብር	ብር	ብር		
6116	300,000.00	189,663.01	110,336.99		37	ለሠራተኞች ሰርቪስ የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ጋርዥ በመግባታቸው ለሾፌሮች ለረዳት ያለተከፈለ በመሆኑ ነው፡፡
6131	4,678,134.48	4,849,190.90		171,056.42	4	በበጀት ዓመቱ የ6111 በጀት እጥረት በመፈጠሩ ተጨማሪ በጀት ጥያቂ ቀርቦ ሲጸድቅ አብሮ ባለመጠየቁ ምክንያት ነው፡፡
6212	400,000.00	315,200.11	84,799.89		21	የገንዘብ ጥያቄ ቀርቦ በወቅቱ ባለመለቀቁ ክፍያ መፈጸም ባለመቻሉ ምክንያት ነው፡፡
6215	800,000.00	689,759.70	110,240.30		14	የማዕቀፍ ግዥ ዘግይቶ በመድረሱና የገንዘብ ጥያቄ በወቅቱ ባለመለቀቁ ምክንያት ነው፡፡
6217	2,400,000.00	1,878,589.46	521,410.54		22	ለመማር ማስተማር የሚውሉ የእርሻ ማሽነሪዎች በብልሽት ምክንያጥ በቂ እርሻ መታረስ ባለመቻሉ ነዳጅ ባለመጠቀማችን በጀቱ ሊተርፍ ችሏል ፡፡
6218	1,000,000.00	861,767.12	138,232.88		14	የማዕቀፍ ግዥ ዘግይቶ በማምጣቱ ምክንያት ነው፡፡

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት				የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ
		ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	በላይ የወጣ	በፐርሰንት በ(%)	
6219	500,000.00	341,427.83	158,572.17		32	ጨረታ ወጥቶ በቂ እቃ በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡
6245	1,200,000.00	1,062,050.21	137,949.79		11	ጨረታ ወጥቶ በቂ እቃ በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡
6313	400,000.00	332,693.00	67,307.00		17	ጨረታ ወጥቶ በቂ እቃ በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡
6314	805,350.00	397,834.80	407,515.20		51	ጨረታ ወጥቶ በቂ እቃ በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ነው፡፡
6315	100,000.00	18,480.00	81,520.00		82	ለመማር ማስተማር የሚውሉ እንስሳት ግዥ ተከናውኖ የቀሩ ስለነበር በበጀት ዓመቱ ግዥ ባለመከናወኑ ምክንያት ነው፡፡
6232	100,000.00	37,982.64	62,017.36		62	የኮሌጁ ቋሚ ሠራተኞች የመስክ ስራ ሲወጡ በኮሌጁ ተሽከርካሪዎች በመጠቀማቸው ነው፡፡
6251	1,600,000.00	1,391,793.97	208,206.03		13	የተማሪዎች ምዘና የሚሠጠው የኦሮሚያ ልዕቀት ማዕከል ከተማሪዎች ፕሮግራም ጋር በመዛባቱ ሊከፈል ባለመቻሉ ነው፡፡
6253	100,000.00	45,212.01	54,787.99		55	ግዥዎች በአብዛኛው በማዕቀፍ ግዥ በመከናወኑ የጨረታ ማስታወቂያ ባለመወጣታችን ምክንያት ነው፡፡
6254	250,400.00	213,904.07	36,495.93		15	ተሽከርካሪ ለጥገና ጋራዥ ገብቶ በመቆየቱ ለኢንሹራንስ መከፈል የሚገባውን ክፍያ

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት				የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ
		ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	በላይ የወጣ	በፐርሰንት በ(%)	
						ባለመፈጸሙ ምክንያት ነው፡፡
6255	165,333.34	23,100.00	142,233.34		86	አብዛኛዎቹ ግዥዎች በማዕቀፍ በመሆናቸው በኮሌጁ ተሽከርካሪ በማጓጓዥ ምክንያት ለሌላ ተሽከርካሪዎች ወጪ ባለመውጣቱ ምክንያት ነው፡፡
6256	220,000.00	183,459.45	36,540.55		17	በ 2009 በጀት ዓመቱ ለመኪና ቦሎ ወጪ ሆኖ ነገር ግን ሂሳቡ በ2010 በጀት ዓመት በመወራረዱ ምክንያት ነው።
6258	640,500.00	235,697.86	404,802.14		63	በ2009 በጀት ዓመት የኢንተርኔት ክፍያ ከቴሌ ባለማቅረቡ ያልተከፈለ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡
6259	7,000.00	538.01	6,461.99		92	የውሃ አገልግሎት ክፍያ በውሃ መቋረጥ ምክንያት ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡
6323	3,300,000.00	1,506,269.15	1,793,730.85		54	ተቋራጩ የክፍያ ሠነድ ባለማቅረቡ ምክንያት ነው።
ድምር	18,966,717.82	14,574,613.30	4,563,160.94	171,056.42		
I. ከውስጥ ገቢ የወጪ በጀት						
6114	4,458,472.00	2,685,498.50	1,772,973.50		40	
6116	350,000.00	148,865.67	201,134.33		57	
6211	28,280.00		28,280.00		100	

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት				የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ
		ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	በላይ የወጣ	በፐርሰንት በ(%)	
6212	23,490.00	12,005.76	11,484.24		49	
6213	7,180.00	720.00	6,460.00		90	
6214	200,000.00	99,604.22	100,395.78		50	
6217	438,900.00	38,302.68	400,597.32		91	
6218	2,100,000.00	997,468.26	1,102,531.74		53	
6219	849,810.00	3,350.00	846,460.00		99.6	
6221	1,300,500.00	109,561.00	1,190,939.00		92	
6222	400,220.00	29,720.90	370,499.10		93	
6223	50,000.00		50,000.00		100	
6241	228,200.00	194,615.82	33,584.18		15	
6243	100,000.00	6,599.19	93,400.81		93	
6244	72,500.00	52,331.05	20,168.95		28	
6245	115,000.00		115,000.00		100	
6311	516,100	455,400	60,700		12	
6313	1,776,000.00	615,652.95	1,160,347.05		65	
6314	27,800.00		27,800.00		100	
6315	2,500,000.00	888,700.00	1,611,300.00		64	
6231	561,000.00	443,470.18	117,529.82		21	
6232	35,000.00	2,664.77	32,335.23		92	
6251	350,000.00	11,688.26	338,311.74		97	
6252	100,000.00	4,368.00	95,632.00		96	
6253	45,000.00		45,000.00		100	
6254	90,000.00		90,000.00		100	
6255	281,000.00	27,105.00	253,895.00		90	

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት				የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ
		ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	በላይ የወጣ	በፐርሰንት በ(%)	
6256	30,000.00	15,592.96	14,407.04		48	
6258	150,000.00		150,000.00		100	
6271	750,000.00	161,439.33	588,560.67		78	
6321	500,000.00		500,000.00		100	
ድምር	18,434,452.00	7,004,724.50	11,429,727.50			
ጠቅላላ ድምር	37,401,169.82	21,579,337.80	15,992,888.44	171,056.42		

<u>በፋይናንስ መመሪያውና በውሉ በተመለከተው መሰረት ያልተመዘገበናያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ ዝርዝር፤</u>

I. ክፍያው የተፈጸመው ፡ አፈወርቅ ግደይ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ (የቢሮ ህንጻ ግንባታ)									
ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	በመስሪያ ቤቱ ሂሳብ ክፍል በየደረጃው ክፍያ ሲፈጸም የተመዘገበ							
		በዴቢት			በክሬዲት				
		6323	4251	Reason	5059	5006	5061	4251	4103
28/10/05	28661	1,996,182.81		Advance payment	260,371.67	15,622.30			1,720,188.84
13/02/06	28912	2,896,546.70		Advance payment	377,810.43	22,668.62			2,496,067.65
30/10/06	581405	1,637,442.36		1ST payment	299,989.44	39,998.59			1,297,454.33
28/11/06	581501	1,105,292.66		2nd payment	144,168.61	19,222.48			941,901.57
27/02/07	581432	908,067.58		3rd payment	118,443.60	15,792.48			773,831.50
27/06/07	581984	2,001,830.21		4th payment	261,108.29	34,814.44			1,705,907.48
04/10/07	582166	611,584.77		5th payment	79,771.92	10,636.25			521,176.60
13/12/07	582374	1,281,707.90		6th payment	167,179.29	22,290.57			1,092238.04
06/04/08	582612	744,160.76		7th payment	97,064.44	12,941.92			634,154.40
28/10/08	065950	1,045,001.65		8th payment	136,304.56	18,173.94			890,523.15
ድምር		14,227,817.40			1,942,212.25	212,161.59			12,073,443.56

II. ክፍያው የተፈጸመው ድርጅት ሥም ፡ አፈወርቅ ግደይ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ (የቢሮ ህንጻ ግንባታ)									
አጠቃላይ ውል የተገባበት የኮንትራት ክፍያ		የወጪው ምክንያት	የቅድሚያ ክፍያው ሲፈጸምና ለተሰራው ሥራ ክፍያ ሲፈጸም መከናወን የነበረበት ምዝገባ						
የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ሳይጨምር	የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ		በዴቢት		በክሬዲት				
			6322	**4251**	**5059**	**5006**	**5061**	**4251**	**4103**
14,181,824.68	**16,309,098.38**	**Advance payment 30%**		4,892,729.51	638,182.11				4,254,547.40
ሥራው ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አስከ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ለተሰሩ ሥራዎች የተፈጸመ አጠቃላይ ክፍያ			14,560,911.05	0.00	1,329,474.49	212,161.59	633,083.09	4,892729.51	7,493,462.37
ድምር			14,560,911.05	4,892,729.51	1,967,656.60	212,161.59	633,083.09	4,892,729.51	11,748,009.77

II. ማጠቃለያ								
ክፍያው የተፈጸመው ድርጅት ሥም ፡ አፈወርቅ ግደይ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ (የቢሮ ህንጻ ግንባታ)								
የሒሳቡ መደብ	በመስሪያ ቤቱ ሂሳብ ክፍል በየደረጃው ክፍያ ሲፈጸም የተደረገ አጠቃላይ ምዝገባ		ሊሆን የሚገባው ምዝገባ		ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት የሚገባ ሂሳብ			ምርመራ
	ዴቢት	ክሬዲት	ዴቢት	ክሬዲት	የሒሳቡ መደብ	ዴቢት	ክሬዲት	
6323	14,227,817.40	0.00	14,560,911.05		6323	333,093.65	0.00	በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ በመሆኑ ነው፡፡
5059	0.00	1,942,212.25	0.00	1,967,656.60	5059	0.00	25,444.35	ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ በመሆኑ ነው፡፡
5006	0.00	212,161.59	0.00	212,161.59	5006			
4251	0.00	0.00	4,892,729.51	4,892,729.51	4251	0.00	0.00	
5061	0.00	0.00	0.00	633,083.09	5061	0.00	633,083.09	ተቀንሶ ያልተመዘገበና ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ በመኖሩ ነው፡፡
4103	0.00	12,073,443.56	0.00	11,748,009.77	4103	325,433.79	0.00	ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በመሆኑ ነው፡፡
ድምር	14,227,817.40	14,227,817.40	19,453,640.56	19,453,640.56		658,527.44	658,527.44	

አባሪ. 6

<u>በብልሽት ለሚገኙት ዕቃዎች የፎቶግራፍ አባሪዎች</u>

F 155R
FAUN FRISCH

Spreader
OFF-ROAD

<u>በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር</u>

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ___________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ___________________________

የተዘጋጀበት ቀን፡ - ___________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።